“እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ...........” 2ኛ ተሰሎንቄ 2:15

JUNE 2018

# በ 2ኛው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች መሰረት የተዘጋጀ የመጽሓፍ ቅዱስ ማጥኛ ደብተር

ስም፡...............................................................................................................................

የመድኃኒዓለም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን - ሰይንት-ሉዊስ
የትምህርት ክፍል ያዘጋጀው

-----------------------------------------------------------------------------------------

## 1. መግቢያ

ሐዋርያ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያን በፃፈው የመጀመርያው መልዕክቱ: የቤተ-ክርስቲያኒቱ: አማኞችን: ለጌታ ስላሳዩት ታማኝነት እንዳመሰገናቸው: በእምነታቸው እንዲጸኑና ጌታንና መንገዱን በማወቅ የበለጠ እንዲያድጉ እንዳበረታታቸው አጥንተናል። የተሰሎንቄ ሰዎች: በእምነትና በፍቅር እንዳደጉ፡ በጌታም ተስፋ መጽናትን እንደተማሩ፡ ከዚህም የተነሳ መልካም ምስክርነት እንደያዙና፡ በቁጥርም እየበዙ እንደነበረ መስክሮላቸዋል። የጌታን መምጣት በመጠባበቅም፡ የቤተ-ክርስቲያኒቱ: አማኞች: በመንፈሳዊ ሂወታቸው እንዲያድጉ መንገዱን እንዳሳያቸውና እንደመከራቸው: አጥንተናል። መልዕክቱ: በዚህ ዘመን ለምንኖር አማኞችም ህይወት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ እንዴት መኖር እንደምንችልና: የጌታን መምጣት ተስፋ በማድረግ እንዴት በእምነታችን መጽናትና በቅድስና መኖር እንደምንችል አስተምሮናል።

ሁለተኛው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች: ከመጀመርያው መልዕክቱ ጋር የተያያዘ ነው። ሐዋርያው ከምስጋናና ጸሎት በተጨማሪ የተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያንና ምእመኖቿ በመንፈሳዊ ሂወታቸውና

አገልግሎታቸው: እንዲቀጥሉ: እንዲጸኑና: እንዲያድጉ: የሚያስፈልግ: መንፈሳዊ ምክርና ትምህርት ያካተተ መልዕክት ነው።

## 2. የመልዕክቱ ዓላማ

የተሰሎንቄ ሰዎች: ምንም እንኳ በእምነት፡ በፍቅርና፡ በጌታ-ተስፋ እየበረቱና እያደጉ ቢመጡም፡ ይደርስባቸው የነበረው ስደትና መከራ በዛው መጠን፡ እያየለ መጥቷል። ከዚህም የተነሳ: በመካከላቸው የእምነት መናወጥና ድንጋጤ: እንዲሁም ስለ ጌታ ተመልሶ መምጣት የተሳሳተ ትምህርት መታየት ጀምሯል:: "የጌታ ቀን ደርሷል ብሎ ጳውሎስ በመልዕክት ተናግሯል" የሚል ትምህርት በአንዳንድ ሰዎች በኩል ወደ: ቤተ-ክርስቲያኒቱ: ሰርጎ እንደገባም ሐዋርያው ሰምቷል። ሐዋርያው: የተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያንና የምእመናቿ ጉዳይ በጣም ስላሳሰበው፡ ይህችን ሁለተኛይቱን መልዕክቱን:

1. **የጌታን መምጣት መጠባበቃቸውን እንዲቀጥሉና በመከራቸው ሁሉ እንዲጸኑ ለመምከርና ለማጽናናት**

2. **ስለ ጌታ መምጣት ትክክለኛ የሆነ መረዳት እንዲኖራቸውና በስህተት የገባውን ትምህርት ለማረም**
3. **ሐዋርያ ጳውሎስንና ሌሎቹን ታማኝ አገልጋዮችን በመምሰል ለሚያያቸው ሁሉ ጥሩ ምሳሌ እንዲሆኑ ለማስተማር**

ይጽፍላቸዋል።

ሁለተኛ ተሰሎንቄ: በዚህ ዘመን ለምንኖር አማኞችም: 1) **በመከራ ለምን መጽናት እንደሚገባን፡ 2) ስለ ጌታ መምጣት ማወቅ ያለብን ነገሮች: እንዲሁም 3) ጌታን እየተጠባበቁ መኖር፡ ምን ያህል ለዕለታዊ ክርስቲያናዊ ኑሮአችን ጠቃሚ እንደሆነ** ያስተምረናል። ለዚህ እንዲረዳን ትምህርቱን እነዚህን 4 ነገሮች እያሰብን እናጠናዋለን።

1. የማጠናው የመጽሓፍ ቅዱስ ክፍል፡ ስለ እግዚአብሔር ምን ይናገራል? ይህ ማለት የእግዚአብሔር ማንነትን፡ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ አሰራርን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

2. የማጠናው የመጽሓፍ ቅዱስ ክፍል፡ ስለ ሰውስ ምን ይናገራል? ይህ ስንል በክፍሉ የተገለጡት ሰዎች የሚያሳይቱ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ (ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተ ድርጊትን የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።
3. ከማጠናው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዛሬ እኔ ምን አዲስ ነገር እማራለሁ? በዚህ ጊዜ: የተማርነው ነገር: ሌሎች እንዲማሩበት ለጥናት አባሎች ሃሳቡን ማካፈል አለብን።
4. በተማርኩት የእግዚአብሔር ቃል መሰረት፡ በመንፈሳዊ ሕይወቴ ለማደግ ምን ማድረግ አለብኝ?

መልካም ጥናት!

# ጥናት ቁጥር 01

**የንባብ ክፍል፡** 2ኛ ተሰሎንቄ 1:1-4

1 ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር በአባታችን
በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ
ክርስቲያን፤ 2 ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ
ሰላምም ለእናንተ ይሁን። 3 ወንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ
ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ፥
ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን 4
ስለዚህ በምትታገሱበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና
ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ
ራሳችን እንመካለን።

1. በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:2 “ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።” የሚል እናነባለን። በእግዚአብሔር ጸጋና በእግዚአብሔር ሰላም መካከል ምን ልዩነት አለ ይላሉ?

............................................................................................................................................................

............................................................................................................................................................

............................................................................................................................................................

............................................................................................................................................................

ለ. ሐዋርያ ጳውሎስ: በመልዕክቶቹ "ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን" የሚለውን ሃሳብ በተደጋጋሚ ሲጠቀም እናነባለን። ይህ ለምን የሆነ ይመስልዎታል?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

2. በተሰሎንቄ 2:1-4 መሰረት ስለ ሰው (ሰዎች የሚያሳይቱ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ ድርጊትን - ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተን) ፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል) ምን ያነባሉ?

............................................................................................................................................

............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

3. ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 1:2-3 *"…….የእምነታችሁን ስራ የፍቅራችሁንም ድካም በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን…….*" በማለት ሲጽፍ: በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:3-4ግን **"‚‚‚‚‚‚እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን፤ ስለዚህ በምትታገሱበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ ራሳችን እንመካለን….."** ብሎ ይጽፋል? (ለበለጠ ማብራሪያ አዲሱን እትም ይመልከቱ)

ሀ. በነዚህ ሁለት ሃሳቦች ምን ልዩነት ይመለከታሉ?

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

.............................................................................................................................................................................

.............................................................................................................................................................................

ለ. የተሰሎንቄ ሰዎች: በእምነት ማደጋቸው: በእርስ በርስ ፍቅር መጨመራቸውና በመከራ መጽናታቸው ምክኒያቱ ምን ይመስልዎታል?

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

4. “ስለዚህ በምትታገሱበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ ራሳችን እንመካለን።” የሚለውን ሃሳብ እንዴት ይረዱታል?

.............................................................................................................................................................................

.............................................................................................................................................................................

.............................................................................................................................................................................

.............................................................................................................................................................................

5. ከዛሬው ትምህርት ምን አዲስ ነገር ተማሩ? የተማሩትን በህይወትዎ እንዴት ለመጠቀም ያስባሉ?

.................................................................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 02

**የንባብ ክፍል፡** 2ኛ ተሰሎንቄ 1:5-12

5 ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት
የምትበቁ ሆናችሁ ትቈጠሩ ዘንድ፥ ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት
ነው። 6-7 ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት
ነበልባል ሲገለጥ፥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን፥ መከራንም ለምትቀበሉ
ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት
በእርግጥ ጽድቅ ነውና። 8 እግዚአብሔርን የማያውቁትን፥ ለጌታችንም
ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤ 9 -10 በዚያም ቀን
በቅዱሳኑ ሊከብር፥ ምስክርነታችንንም አምናችኋልና በሚያምኑት ሁሉ
ዘንድ ሊገረም ሲመጣ፥ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም
ጥፋት ይቀጣሉ። 11-12 ስለዚህም ደግሞ እንደ አምላካችን እንደ ጌታም
እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእናንተ
ዘንድ ሊከብር እናንተም በእርሱ ዘንድ ልትከብሩ፥ አምላካችን ለመጥራቱ
የምትበቁ አድርጎ ይቈጥራችሁ ዘንድ፥ የበጎነትንም ፈቃድ ሁሉ

የእምነትንም ሥራ በኃይል ይፈጽም ዘንድ ስለ እናንተ ሁልጊዜ እንጸልያለን።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (2ኛ ተሰሎንቄ 1:5-12) ስለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ማንነትን፡ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ አሰራርን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል) ምን ይናገራል?

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

ለ. በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:5 "......ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት ነው" የሚል እናነባለን። እግዚአብሔር ከባህርዩ አንዱ ቅን ፈራጅ መሆኑ ነው። ይህንን ሃሳብ እንዴት ይገልጹታል?

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

2. በዚሁ በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:5-12 ስለ ሰው [ይህ ስንል በክፍሉ የተገለጡት ሰዎች የሚያሳይቱ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተ ድርጊትን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል] ምን ያነባሉ?

................................................................................................................................................................

................................................................................................................................................................

................................................................................................................................................................

................................................................................................................................................................

ለ. በክፍሉ መሰረት፡ ለሚከተሉት ሰዎች ጌታ ኢየሱስ እንደገና ሲመጣ የሚደርስባቸው ምንድ ነው? ልዩነታቸውስ ምንድ ነው?

**1. እግዚአብሔርን የማያውቁትን**

**2. ወንጌል የማይታዘዙትን**

**3. ለጌታ ሲሉ መከራ የሚቀበሉትን**

3. የተሰሎንቄ ሰዎች: ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁዎች ሆነው እንደተቆጠሩ ጳውሎስ መስክሮላቸዋል። ጳውሎስ ይህን ምስክርነት የሰጠበት ምክኒያት ምንድ ነው?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

ለ. ዛሬ እርስዎ ለእግዚአብሔር መንግሥት የምበቃ ነኝ ብለው ያስባሉ? ለምን?

................................................................................................................................

................................................................................................................................

................................................................................................................................

................................................................................................................................

ሐ. በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:5 ያለው ሃሳብ: በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1:12 ካለው ያሳብ ጋር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

..............................................................................................

# ጥናት ቁጥር 03

**የንባብ ክፍል፡** 2ኛ ተሰሎንቄ 2:1-12

1-2 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት፡- የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፥ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን። 3 ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና። 4 እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው። 5 ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፥ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁምን? 6 በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ። 7 የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። 8 በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ 9-10

ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። 11-12 ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (2ኛ ተሰሎንቄ 2:1-12) ስለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ማንነትን፡ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ አሰራርን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል) ምን ይናገራል?

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

2. በዚሁ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:1-12 ስለ ሰው [ይህ ስንል በክፍሉ የተገለጡት ሰዎች የሚያሳይቱ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተ ድርጊትን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል] ምን ያነባሉ?

4. በጥናት ክፍሉ መሰረት ጳውሎስ የስህተቱን ትምህርት ለማስተካከል፡ "....ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤......" ካለ በኋላ፡ የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት መሆን ያለባቸው ሶስት ነገሮች ይነግራቸዋል። እነዚህ ምንና ምን ናቸው?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

5. በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:6-7 “ በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ። የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።” የሚል እናነባለን። በጳውሎስ መሰረት፡ ዓመፀኛው፡ እንዳይገለጥ፡ የሚከለክለው ምንድ ነው?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

ለ. “....የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤” ሲልስ ምን ማለቱ ነው?

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

6. በቍጥር 9-10 “ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።” የሚለውን የጳውሎስ አባባል እንዴት ይረዱታል?

........................................................................................................................

........................................................................................................................

........................................................................................................................

........................................................................................................................

7. ከዚህ የጥናት ክፍል የቀረልዎት ምን ትምህርት አለ?

........................................................................................................................................................

..................................................................................................................___________________

_______________________________________________________________________________________

# ጥናት ቁጥር 04

**የንባብ ክፍል፡** 2ኛ ተሰሎንቄ 2:13-17

13 እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ
እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ
እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤ 14 ለዚህም
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ። 15
እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም
በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ። 16-17 ራሱ ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስና የወደደን በጸጋም የዘላለምን መጽናናት በጎንም ተስፋ የሰጠን
እግዚአብሔር አባታችን ልባችሁን ያጽናኑት በበጎም ሥራና በቃል ሁሉ
ያጽኑአችሁ።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (2ኛ ተሰሎንቄ 2:13-17) ስለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ማንነትን፡ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ አሰራርን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል) ምን ይናገራል?

4. ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:13 "እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት **መርጦአችኋልና**" ሲል **ምርጫ** የሚለውን ሃሳብ እንዴት ይረዱታል?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................

ለ. **ምርጫ** ካለ ታዲያ **ወንጌልን መመስከር** ለምን አስፈለገ ይላሉ?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

...............................................................................................................................................

ሐ. በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:13-14 ያለው ሃሳብ: ሮሜ 8፡29-30 ካለው ሃሳብ ጋር እንዴት ይመሳሰላል??

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 05

**የንባብ ክፍል፡** 2ኛ ተሰሎንቄ 3:1-5

1-2 በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ። 3 ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው። 4 የምናዛችሁንም አሁን እንድታደርጉ ወደ ፊትም ደግሞ እንድታደርጉ ስለ እናንተ በጌታ ታምነናል። 5 ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትዕግሥት ልባችንን ያቅናው።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (2ኛ ተሰሎንቄ 3:1-5) ስለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ማንነትን፡ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ አሰራርን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል) ምን ይናገራል?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

ለ. በ2ኛ ተሰሎንቄ 3:3 “.......... ጌታ የታመነ ነው” የሚል እናነባለን። እግዚአብሔር ከባህርዩ አንዱ ታማኝ መሆኑ ነው። በቅርቡ፡ እግዚአብሔር ለርስዎ ታማኝነቱን ያሳየበት ሁኔታ አለ? ካለ ለጥናት ቡድንዎ ያካፍሉ።?

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

2. በዚሁ በ2ኛ ተሰሎንቄ 3:1-5 ስለ ሰው [ይህ ስንል በክፍሉ የተገለጡት ሰዎች የሚያሳይቱ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተ ድርጊትን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል] ምን ያነባሉ?

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

...............................................................................................................................................

3. ጳውሎስ በቁጥር 1ና2፡ የተለያዩ የጸሎት ጥቅሞችን ጽፎልናል። እነዚህ ምናን ምን ናቸው?

# ጥናት ቁጥር 06

**የንባብ ክፍል፡** 2ኛ ተሰሎንቄ 3:6-18

6 ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት
ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
እናዛችኋለን። 7 እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ
ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፤ 8 ከእናንተ
ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት
እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም። 9
ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር
እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም። 10 ደግሞ ከእናንተ ጋር
፡-ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። 11 ሥራ ከቶ
ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ
አንዳንዶች ሰምተናልና። 12 እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ
እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን
እንመከራቸውማለን። 13 እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን
ለመሥራት አትታክቱ። 14 በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ

ማንም ቢኖር፥ ይህን ተመልከቱት፥ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር አትተባበሩ።
15 ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ ጠላት አትቍጠሩት። 16
የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉ መንገድ ዘወትር ሰላምን ይስጣችሁ። ጌታ
ከሁላችሁ ጋር ይሁን። 17 በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ
ነው፤ የመልእክቴ ሁሉ ማስረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ። 18 የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (2ኛ ተሰሎንቄ 3:6-18) ስለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ማንነትን፡ ባህርይን፡ አስተሳሰብን፡ አሰራርን፡ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል) ምን ይናገራል?

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

ለ. ጳውሎስ በ ቁጥር 6 ና 12 "...በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን: የሚል ጽፏል። ይህ ሃሳብ ምን ማለት ነው? በአማኞች መካከልስ እንዴት ነው የሚሰራው?

ለ. ጳውሎስ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ብሎ ያቀረበው ሃሳብ ምንድ ነው?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

4. በዚህ የንባብ ክፍል መሰረት: ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለስርአት የሚመላለስ ሰው ቢኖር፡ ቤተክርስቲያን ማድረግ ያለባት ምንድ ነው?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

5. ጳውሎስ በቁጥር 11-12 *“ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ*

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። ”

ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

6. “የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉ መንገድ ዘወትር ሰላምን ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።” የሚለውን ሃሳብ ከመልእክቱ ጋር እንዴት ይረዱታል?

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

7. ጳውሎስ በቁጥር 17 “ በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው፤ የመልእክቴ ሁሉ ማስረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ።” ብሎ መጻፍን ለምን አስፈለገው?

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................

.......................................................................................................................................


The Thessalonians' False Idea
The Rapture
WE ARE HERE
Jesus' Second Coming
CHURCH AGE
TRIBULATION
MILLENNIUM


Paul's Correction of their Error
YOU ARE HERE
The Rapture
Restrainer removed
Jesus Second Coming
The Apostasy
Antichrist Revealed
Antichrist Destroyed
CHURCH AGE
TRIBULATION
MILLENNIUM